# እነሆ፥ ሙሽራው እየመጣ ነው!

በ ቦኒ ጆንስ - **By Bonnie Jones**

ሜይ 2015 (በኢትዮጵያ አቆጣጠር በግንቦት 2007 ዓ.ም ጌታ ራእዩን አሳየ)



በአንድ ራእይ አንድ ባለጸጋ የንግድ ሰው እናቴን በቤቷ ሊጎበኛት ሲመጣ አየሁ። የመገኘቱን እውነታ አረጋገጥሁ፥ ነገር ግን ወደ ክፍሌ እንዳይገባና በእንግዶች እንዳይታወቅ ራሴን ነቀነቅሁ ምክንያቱም እርሱ ያገባ ሰው እንደሆነ አውቄ ነበርና። ልክ ሲዞርና በሌላኛው መንገድ ሲራመድ ፈገግ አለ።

እናቴ ቤተክርስቲያንን እንደምትወክልና ነጋዴውም እርሷን ለማግባት የሚመጣው **ጌታ** እንደሆነ አምናለሁ። **እርሱ**ም የመንግሥቱን ባለጠግነት(ሀብት፥ ብልጽግና) ከእርሱ ጋር ይዞ እየመጣ ነው። እርሱ የሚመጣው በደህና የተቀበሉት ጋር ብቻ ነው **He** will only coming to where **He** is welcomed። ራሳቸውን ዝግጁ ላደረጉ ለእነዚያ “ቆንጆ (ድንግል)” ቤተክርስቲያኖች **እርሱ** እየመጣ ነው። እነርሱ ዘይቱን በመብራታቸው ውስጥ አዘጋጅተዋል እና **በእርሱ**(**በጌታ በክርስቶስ ኢየሱስ**) እንዴት ማረፍ እንደሚቻል ተምረዋል። ***(ማቴዎስ 25:1-13)***

በ**ጌታ** ለመጎብኘት አንድ ዓይነት አጋጣሚ(ዕድል) ያላቸው አሥር ደናግላን(ቆነጃጅት) ነበሩ ሆኖም አምስቱ ሰነፎች ነበሩ ጥቂትም ዝግጅት አደረጉ። መንፈሳዊ ብስለትን አካል እንዳያገኝ እየከለከሉ በሰው ዓይን ጥሩ ሆኖ መታየትና ሃይማኖትም

አጥብቀው መያዝ ቀጠሉ - They continued looking good in the eye of man and held on to religion depriving the body its spiritual maturity። ሌሎቹ አምስት ቆነጃጅት ግን ጠቢብ(ልባም) ሆነው ሳሉ በሰነፎቹ (በሚደርስባቸው) መከራን ተሠቃዩ። ሆኖም እነርሱ(ልባሞቹ ደናግላን) በ**መንፈስ ቅዱስ** ስጦታዎች፣ በ**ቃሉ**ም ስር መስደድና **ማፍቀር**ም ተምረው መብሰል ቀጠሉ።

> *ከእነርሱም አምስቱ ሰነፎች አምስቱም ልባሞች ነበሩ። ሰነፎቹ መብራታቸውን ይዘው ከእነርሱ ጋር ዘይት አልያዙምና፤ ልባሞቹ ግን ከመብራታቸው ጋር በማሰሮአቸው ዘይት ያዙ። ሙሽራውም በዘገየ ጊዜ ሁሉ እንቅልፍ እንቅልፍ አላቸውና ተኙ።* **(*ማቴዎስ* 25:2-5)**

እነሆ፥ ሙሽራው እየመጣ ነው! የጉብኘት ጊዜ አይደለም። **እርሱ** ቤተክርስቲያንን ለማግባት እየመጣ ነው! ለኢሳይያስ 62፥3-4 ጋብቻ እየተዘጋጀን ነው ምክንያቱም **አብ** ይህንን ጋብቻ እየባረከው ነው። ከእንግዲህ ወዲህ ቤተክርስቲያን የተተወች አትባልም፥ **እግዚአብሔር** በእርሷ ተደስቶአልና እርሷ(ቤተክርስቲያን) ደስታዬ የሚኖርባት (ሄፍዚባህ) ትባላለሽ።

> *በእግዚአብሔር እጅ የክብር አክሊል፥ በአምላክሽም እጅ የመንግሥት ዘውድ ትሆኛለሽ። ከእንግዲህ ወዲህ። የተተወች አትባዪም፤ ምድርሽም ከእንግዲህ ወዲህ። ውድማ አትባልም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በአንቺ ደስ ብሎታልና፥ ምድርሽም ባል ታገባለችና አንቺ። ደስታዬ የሚኖርባት ትባያለሽ ምድርሽም። ባል ያገባች ትባላለች።* **(*ኢሳይያስ* 62:3-4)**

**አብ** ቤተክርስቲያኑን እርሷ ከምታስበው በላይ ሊባርካት እየተዘጋጀ ነው። ዓለም ሁሉ እንዲያይ እርሷም በ**እርሱ** እጅ የክብር አክሊል ትሆናለች። በ**እርሱ** ኃይልና ክብር የተነሣች የቤተክርስቲያን ጋብቻ ይህ ነው። ጆን ዌስሊ "በእሳት ተያያዙ ሌሎችም እናንተ ስትነድዱ ለማየት መምጣት ይወዳሉ።" *"Catch on fire and others will love to come watch you burn."* ይል ነበር። **ወልድ** የራሱን ሙሽራ ሲስም እርሷ በእሳት ትያያዛለች የ**እግዚአብሔር** ክብርም አይሳሳትም። ሰዎች ክብሩን ለመመስከር ከቅርብም ከሩቅም ይመጣሉ። ያን ንጉሣዊ የክብር አክሊል በትክክል(ደረጃ) እንድንሆን ነው **አብ** ባህሪያችን(ጠባያችን) ላይ እየሠራ ያለው።

## የጥበብ መወለድ - Birthing of Wisdom

ጥበብ በ"ልባም(ጠቢብ) ድንግል" ቤተክርስቲያኖች ተይዞአል፤ ነገር ግን የበለጠ ጥበብ ከዚህ የክብር አክሊል ውስጥ ይወለዳል። የዘላለምን በር ለመክፈት ቁልፉ ጥበብ ነው። ጸጋ ያስገባችኋል። ሞገስ ወደ መረዳት የሰውን ልብ ይከፍታል እና የ**እግዚአብሔር** እውነትም የመንግሥተ ሰማይን በር ይከፍታል። **ጌታ** የሚያገባት "ልባም(ጠቢብ) ድንግል" ቤተክርስቲያኖች ውስጥ እየሠራ ያለው መሻሻል ይህ ነው። **እርሱ** እርሷን ከሰው አረዳድ(መረዳት) በላይና ባሻገር እየወሰዳት ነው። በዚህ የመከር ጊዜ(ሰዓት) መንገዱን ለድኅነት(ለመዳን) ቀጥተኛ የሚያደርገው መሣሪያው ነው። ከግድግዳዎች ውጪ ባለች ቤተክርስቲያን (የእግዚአብሔር ቃል ያዘዛቸውን ሳያደርጉ ሕንጻ ቤተክርስቲያን ውስጥ ብቻ ቁጭ የሚሉ ክርስቲያኖች ሳይሆኑ፥ ልክ ጌታችንና አዳኛችን የእግዚአብሔር ልጅ የዓለም ብርሃን፣ መንገድ እውነትና ሕይወትም የሆነ በከበረ ደሙ መፍሰስ በቀራንዮ መስቀል ላይ ሞቶ የዋጀን፣ በሦስተኛውም ቀን በአባቱ ቅዱስ መንፈስ በራሱም ቅዱስ ፈቃድ ከሙታን ተለይቶ የተነሣው፣ ወደ ቅዱስ አባቱም ያረገው፣ እጅግ በቅርቡም ዳግም የሚመጣው ሰላማችን የነገሥታት ንጉሥ የጌታዎች ጌታ የእግዚአብሔር ቃል እግዚአብሔር የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳደረገውና እንዳዘዘው ትሑትና የዋህ የሆነውን እርሱን ጌታ ኢየሱስን አርአያ አድርገው በየቦታው ሁሉ በየሠፈሩ በየቤቱ በየከተማው በየመንገዱ በየእስር ቤቱ በየመሥሪያ ቤቱ በየሆስፒታሉ በነገሥታት ፊት እስከ ዓለም ዳርቻ ወንጌልን እየሰበኩ ዕለት ዕለት ቃሉን እያደረጉ እግዚአብሔርን በቃሉ እያፈቀሩ በቃሉና በጸሎት በሚኖሩ ትጉሕ ክርስቲያኖች) ሰዎች **የእግዚአብሔርን** ኃይል ይመሰክራሉ። **ሙሽራው** የራሱን ቤተክርስቲያን ሊያገባ እየመጣ ስለሆነ ተዘጋጁ!

Get ready for **the Bridegroom** is coming to marry **His** Church!

# ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።

ስም የሌለው፥ የማይታወቅ፥ ጌታውና አምላኩ በሆነ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸንቶ የሚኖርና የሚታመን፥ ሊያደርግ የሚገባውን ያደረገ አንድ የማይጠቅም ባሪያ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ተረጎመው። ክብር ሁሉ፣ ኃይልም ብርታትና ጥበብም ውዳሴና ምስጋናም፣ ግርማና ሞገስም፣ ዝማሬና እልልታም ማዳንና ቅድስና ለቡሩክ መልካም ቅዱስ የእስራኤል አምላክ ለአባታችን ለእግዚአብሔር አብ ይሁን ለታረደው በጉም ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለቡሩክ ቅዱስ መንፈሱም ብቻ ይሁን አሜን ሃሌ ሉያ። ማራናታ ጌታ ያሑሹዋ ሐማሺያክ የእግዚአብሔር ልጅ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ቶሎ ና አሜን!

http://www.baptizingfire.com , http://fireofgodservants.blogspot.com/ , http://www.thelordshour.com , http://www.choothomas.org , http://www.Jesusministries.org/ , http://www.angeltv.org , http://www.Billygraham.org , http://free.messianicbible.com/ , http://www.levitt.tv/ ,

http://www.divinerevelations.info/amharic , http://www.heavenvisit.com , http://www.tribulation-now.org , http://www.voe.org/ , http://www.sidroth.org , http://repentandpreparetheway.org/ , http://www.shekinahworship.com/ , http://www.theblazingholyfire.com/ , http://www.thelastreformation.com ,

http://www.bobjones.org/ , http://www.annarountree.com/ , http://www.beyondthephysicalrealm.com , http://www.shreveministries.org , http://www.blogtalkradio/tribulation-now , http://www.bullsere.kr/ http://www.blogtalkradio/thelordshour , http://www.blogtalkradio.com/discoveringthetruth

http://www.be4thefire.com/ , http://www.e-sword.net/